# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org የ shengo.derbiaber@gmail.com


ታህሣስ 11፣ 2007 (ዲሴምበር 20፣ 2014)

## በሕዝብ ላይ የሚካሄደውን ቀጣይ ጭፍጨፋ ለማስቆም በጋራ እንነሳ!

በትላንትናው ዕለት የባህርዳር ከተማ ነዋሪዎች የእምነት ቦታ የሆነውን መስቀል አደባባይ እየተባለ የሚጠራውን ቦታ "የቤተክርስያን የታቦት ማደሪያ፣ ንብረትነቱም የቤተ-ክርስቲያን የሆነውን ለግል ባለሀብት ሊሰጥ አይገባውም" በማለት ተቃውሞውን በሰላማዊ መንገድ ለመግለጽ ተሰብሰቦ በነበረው ሕዝብ ላይ የህወሓት/ኢ.ህአዴግ የጸፀጥታ ኃይሎች ተኩስ ከፍተው እስከ ስድስት ሰዎች መግደላቸውንና ብዙዎችንም ማቁሰላቸው ከቦታው የሚደርሱ ዜናዎች ያረጋግጣሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) ይህን መንግሥታዊ ሽብር አጥብቆ ያወግዛል፣ ጉዳት ለደረሰባቸው ቤተሰቦችና ግለሰቦችም የሀዘናቸው ተካፋይ እንደሆነ ይገልጻል።

ማንኛውም ዜጋ አገዛዙ የሚያራምደውን ፖሊሲ መቃወም መሠረታዊ መብቱ ነው። በሕዝብ ዘንድ ታላቅ ክብር ያላቸውን ታሪካዊ የእምነት ቦታወችንና የመሳሰሉትን የጋራ ንብረቶችን ህወሓት/ኢ.ህአዴግ እንደፈለገ የማርከስና የማፈራረስ መብት ከቶውንም የለውም። የዚህን ዓይነት የሕዝብን እምነት፣ ታሪክና አኗኗር ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ወይም ለነዚህ ዓይነት ጉዳዮች ግድየለሽነትን የሚያሳይ የአገዛዙን ተግባራት መቃወም የሕዝብ መብት ብቻ ሳይሆን ታሪካዊም ባህላዊም ግዴታ ነው።

አገዛዙ የሕዝብን የእምነት ማዕከሎችና ሌሎችም ታሪካዊ ቦታዎችን ተንከባክበቦ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ ሃላፊነቱ ነው። ይህንን ሃላፊነቱን በዘነጋ አገዛዝ ላይ ደግሞ በተለያየ መንገድ ተጽእኖ መድረግ ከአንድ ለባህሉ ለታሪኩና ለጋራ እሴቶቹ ከሚቆረቆር ሕዝብ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ከዚህ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ተቃውሞዎች አገዛዙ የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ቆም ብሎ ለመመርመርና የሕዝብን እምነት የሚያስከብር የጋራ እሴቶችንም ለማዳበር የሚያግዝ ከፍተኛ ዕድል አድርጎ ሊመለከተው በተገባ ነበር። ተደጋግሞ እንደሚታየው ግን የአገዛዙ አካሄድ ከስህተት መማር ላይ ያተኮረ ሳይሆን በስህተት ላይ ስህተት መጨመር ነው።

የህወሓት/ኢ.ህአዴግ ገዥዎች የሕዝባችንን እምነትና ታሪክ የሚጻረርና የሚያፈራርስ ተግባር ውስጥ ሲሰማሩ ባህር ዳር የመጀመሪያቸው አይደለም። ለአብነት ለመጥቀስ ያክል፡ ካሁን በፊት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ጣልቃ በመግባት ቤተክርስቲያንን የከፋፈሉ ሲሆን በዋልድባ ገዳም ደግሞ ሰፊ የማፈራራስ ተግባር

ፈጽመዋል። በሙስሊሙ ኅብረተሰብ እምነትም ውስጥ ጣልቃ በመግባትም አፍራሽና እጅግ አደገኛ ተግባር ውስጥ ተዘፍቀው እንደሚገኙ ሁሉም የሚያውቀው ነው።

“ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ” እንደሚባለው፣ ይህ ሁሉ የሚያሳየው የህወሓት/ኢህአዴግ መሪዎች የሀገራችንና የህሕዝባችንን ታሪክና እምነት ምን ያህል እንዳልተገነዘቡት ወይም በንቀትና በጥላቻ እንደሚመለከቱት ነው። እነርሱ እምነትንም፣ ታሪክንም፣ የጋራ እሴትንም ለጊዜው ከሚያግበሰብሱት ጥቅም በላይ እንደሆነ ሊያዩት ከቶውንም አልቻሉም። እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ ዛሬ ይህ ሁሉ ሃላፊነት የጎደለው ፀረ-እምነትና ፀረ-ታሪክ ተግባር የሚፈጸመው የእምነት ሰው ነኝ የሚሉት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስተር በሆኑበት ወቅት መሆኑም ጭምር ነው።

ከሕዝብ የተነጠለው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ “እኔ ያልኩትን ሁሉ እሺ ብላችሁ ተቀበሉ” ከሚል ፍጹም አምባገነን ባህሪ በመነሳት በሃገሪቱ ውስጥ የሚነሳን ማንኛውንም ጥያቄ በጉልበት ጨፍልቆ ለመግዛት የሚያካሂደው መንግሥታዊ ሽብር እየጨመረ እንደመጣ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ የሕዝብን ቁጣ እጅግ ይጨምራል፣ ለታሪኩ፣ ለእምነቱ፤ ለማንነቱና ለመብቱ የሚያደርገውን ትግል እጅግ እንዲጠነክር ያደርገዋል እንጂ ሊያዳፍነው እንደማይችል መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

ቀጣይ የሆነው የህወሓት/ኢህአዴግ የመብት ረገጣና የግፍ ሥርዓት እንዲያከትም፤ በምትኩም አንድነቷ በተጠበቀ ኢትዮጵያ ሥር የሁሉም ዜጋ መብት ተከብሮ እንዲኖር ለማድረግ በጋራ እንነሳ።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**